አፍሪካ ቲቪ

አፍሪካ አካዳሚ
AFRICA ACADEMY

2

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "የልብ ተግባራት"

3

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

## የልብ ተግባራት ከአካላት ተግባራት በብዙ ምክንያቶች ይበልጣሉ፡፡

1) የልብ አምልኮ ሲበላሽ የአካልን አምልኮ ያበላሻል፡፡

- ምሳሌውም ለይዩልኝ መስራትን ይመስል ነው፡፡

2) የልብ ተግባራት ዋና መሰረት ነው፡፡

- በመሆኑም በልብ ሳያስቡት በድንገት የተከሰተ እንቅስቃሴም ሆነ ንግግር በአላህ ዘንድ አያስጠይቅም፡፡

3) የልብ ተግባራት በጀነት ውስጥ ከፍተኛ ማዕረግን የምታስገኝ በመሆኗ ለምሳሌ ዙሁድን ይመስል ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

4) የልብ ተግባራት ከአካል ተግባራት ይበልጥ ከባድ በመሆናቸው ነው፡፡

- ኢብኑል- ሙንከዲር ‹‹ራሴን ለማስተካከል አርባ አመት ጥሬ (ለፍቼ) ነው የተስተካከለችልኝ›› ብለዋል፡፡

5) የልብ ተግባራት ውጤታቸው ሲታይ በጣም የሚያምር በመሆኑ ነው፡፡

- ለምሳሌ የአላህን ውዴታን ይመስል ነው፡፡

6) ምንዳቸውም ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

- አቡ ደርዳእ ‹‹አንዲት ሰዓት መመራመር /ማሰብ/ ለሊቱን ሙሉ ቆሞ ከማደር ይበልጣል›› ብለዋል፡፡

- 7) የልብ ተግባራት ለአካል እንቅስቃሴዎች ሁሉ ቀስቃሽ በመሆኗ ነው፡፡
- 8) የልብ ተግባራት የአካል ተግባራት ዋጋን ከፍ ያደርጋል ያሳንሳልም አለበለዚያም ዋጋ ያሳጣልና ነው፡፡
- ለዚህ ምሳሌው ኹሹእ ነው፡፡
- 9) የልብ ተግባሩ በአካል ከሚሰሩ አምልኮቶች አንዳንድ ጊዜ የምትተካቸው በመሆናቸው ነው፡፡
- ለምሳሌ ገንዘብ ሳይኖረው ሰደቃ ማሰብን ይመስል ነው፡፡

- 10) የልብ ተግባራት የምንዳው ግዝፈት ድንበር የሌለው መሆኑ ነው፡፡
- ለምሳሌ ትእግስት
- 11) ማንም ሰው አካል ተግባሩን ቢያቆም ወይም ቢያቅተው እንኳን ምንዳው
- ቀጣይ በመሆኑ ነው፡፡
- 12) ከአካል ተግባራት በፊትና አብሮም መሆን በመቻሉ የሚሉት ናቸው፡፡

- ልብ አካል ወደ ተግባር ሳይገባ በፊት በብዙ ሁኔታዎች ላይ ያልፋል፡፡
  እነርሱም፡-

1. ለመጀመሪያ ጊዜ በአእምሮ ውስጥ ውል ማለት፤
2. ስለጉዳዩ በቋሚነት ማሰብ፤
3. ጉዳዩን ላድርግ አላድርግ በጭንቅላት ውስጥ ማመላለስ፤
4. ጉዳዩን ወደ መተግበር መዘንበል፤
5. ጉዳዩን በመፈፀም በቁርጥ መወሰን በሚሉት የሚያልፍ ሲሆን፤

- የመጀመሪያዎቹ ሶስቶች በኸይር ከሆነ አጅር የላቸውም፡፡

- በወንጀልም ከሆነ አያስጠይቅም አራተኛው በመልካም ነገር ከሆነ አንዲት ሀሰና ሲያስጥ፤ በመጥፎ ነገር ከሆነ ደግሞ ምንም አይፃፍበትም፡፡
- ግን ይኸው አድኅ ወደ ውሳኔ ከበቃና ለመልካም ከሆነ ምንዳ አለው፡፡
- በጥፋት ላይም ከሆነ ባይተገብረውም እንኳን ወንጀለኛ ይሆናል፡፡
- አላህ ‹‹እነዚያ በነዚያ ባመኑት ሰዎች ውስጥ መጥፎ ወሬ እንደተስፋፋ የሚወዱ ለእነርሱ በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም አሳማሚ ቅጣት አላቸው አላህም ያውቃል፡፡ እናንተ ግን አታውቁም›› ብሏል፡፡

- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሀዲስ ‹‹ሁለት ሙስሊሞች በጦራቸው ከተገባበዙ ገዳዩ ግለሰብም ሆነ ተገዳዩ ግለሰብ የእሳት ናቸው››
- ሲሉ ገዳይስ እሺ ሟች ምን ሆኖ ነው አልኳቸውና እሱም ቢሆን ወንድሙን ለመግደል ጓጉቶ ነበርና ነው›› ብለዋል፡፡

- ወንጀልን ለመተግበር ከወሰነ በኋላ ሳይተገብረው ከቀረ በአራት አይነት ይከፈላል፡፡

1. አላህን ፈርቶ የተወው ከሆነ ምንዳ አለው፡፡
2. ሰዎችን ፈርቶ የተወው ከሆነ መተው የነበረበት ለአላህ ብሎ ሲሆን ለሰዎች ብሎ በመተው ወንጀለኛ ይሆናል፡፡
3. ሁኔታዎች አልመቻቸለት ብሎ የተወውም ከሆነ ለመስራት በመወሰኑ ይጠየቃል፡፡
4. ሁኔታዎችን ሁሉ ተግብሮ ተግባሩ ሳይሳካለት ከቀረም በትክክል እንደፈፀመው ይጠየቅበታል፡፡

- ምክንያቱም ለመፈፀም የሚያበቁት ምክንያቶቹን ፈፅሞ ዋናውን ለመፈፀም አቅም አጥቶ መደናቀፍ ከላይ በተጠቀሰው ሀዲስ እንደተረዳነው ሁሉ ልክ እንደፈፀመው ይጠየቅበታል፡፡
- ተግባር ከውሳኔው ጋር ከሆነ ተግባሩ ቢቀድም ቢዘገይ ይጠየቅበታል፡፡
- መጥፎ ተግባር ፈፅሞ ወደፊትም ባመቸው ቀን ራሱ ያንኑ ተግባር ለማድረግ ከወሰነ ባይተገብረውም በተግባሩ ላይ እንደዘወተረ ይቆጠራል፡፡